# እውነትን ፈልጓት፤ ታገኟታላችሁም!!

## ክፍል ሁለት፤

## ካለፈው የቀጠለ።

በክፍል አንድ ጽሑፍ ውስጥ ለመግለጽ እንደተሞከረው ሁሉ እነዚህ ከእውነት ይልቅ ሃሰትን፤ ከቅንነት ይልቅ ተንኮልና ጭካኔን የመረጡ ጥቂት ካህናት ሕዝበ ክርስቲያኑን ለመከፋፈልና አንዱን ከሌላው ጋር በአስተሳሰብ አለያይቶ ለማጋጨት የማይፈነቅሉት ድንጋይ የለም።

ከዚህም ውስጥ በዚሁ በቅርቡ በፌስ ቡክ ላይ በለቀቁት ጽሑፋቸው በርዕሰ አድባራት ለንደን ደብረ ጽዮን ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የደረሰው ችግር "ሰዎች ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያንን ጠንቅቆ ባለመረዳትና የራሳቸው ትርጉም በመስጠት....." የሚል ጠቅሰዋል።

https://www.facebook.com/photo.php?fbid=1564847010427202&set=pcb.1564847773760459&type=1&theater

ይህንንም ያሉበት ምክንያት ነገሩን ሳይረዳ ሕዝቡ ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን የሚባለው ቃል ብቻ አስፈርቶት ሃይማኖታችንን የሚያረክስና ሕግ የሚጥስ ነገር መጣብን ብሎ እንዲሸማቀቅና የእነሱን ከፋፋይ የሃሰት

መረጃ ብቻ እየተቀበለ እንዲከተላቸው ለማድረግ እንጂ በመሠረቱ ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን የሚባሉት 7 ሲሆኑ እነሡም ምሥጢረ ጥምቀት፤ ንሠሃ፤ ቁርባን፤ ተክሊል፤ ክህነት፤ ቀንዲል እና ምሥጢረ ሚሮን ናቸው።

ይህም ብዙ ሊቃውንት አባቶች ጽፈው ለሕዝብ ባቀረቧቸው መጽሐፍት ላይ ተጽፈው የሚገኙ የኦርቶኮዶክ ተዋሕዶ ሃይማኖትና የቤተ ክርስቲያን ቀኖናዊ ሥርዓቶች እንጂ የቤተ ክርስቲያንን አስተዳደርም ሆነ አሁን በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ለተፈጠረው ችግር ምክንያቶች አይደሉም ሆነውም አያውቁም።

<u>**በዚሁ ጽሑፋቸው ላይ ዛሬ በድንኳን ውስጥ የሚጸልዩት ከአሁን በፊት የድምጽ ማጉያ ይዘው ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ረብሻ በመፍጠር ቅዳሴ ያቋረጡ ናቸው የሚል አሁንም አንደኛውን ክርስቲያን ከሌላው ጋር ለማጋጨት ሲሉ የሃሰት መረጃ አቅርበዋል ።**</u>

<u>***ሕዝበ ክርስቲያን ሆይ የሆነውና እውነታው ግን እንደሚከተለው ነው።***</u>

15 የቤተ ክርስቲያን አገልጋይ ምእመናን ከነ ቤተ ሰቦቻቸው ሲቆጠሩ ወደ 40 የሚጠጉ ክርስቲያኖች በስደት ሃገር ሃገሬም ቤተ ክርስቲያኔም ከሚሉት ከአገለገሉበት የእግዚአብሔር ቤት ሆነ ተብሎ በአብይ ጾም መያዣ የቅበላ

ዕለት ለማስቀደስ ቤተ ክርስቲያን እንዳይገቡ አባ ግርማና አጋሮቻቸው በደብዳቤ አገዷቸው።

እግዚአብሔር ያሳያችሁ፤ ክርስቲያኖቹ እቤተ ክርስቲያን ቅጥር ግቢ እንዳይደርሱ የታገዱት የበጎች እረኛ ተብለው የምንኩስናና የቅስና ቆብ በጫኑ፤ የክርስቶስን መስቀል በያዙ ካህናት ሆኖ የታገዱትም ራሳቸውና ቤተ ሰቦቻቸውን ይዘው ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ከማስቀደሰ፤ ከመጸለይና ከማምለክ መብታቸው ነው።

እገዳውንም ለማስፈጸም የባዕድ ሴኩሪቲ በመቅጠር የቤተ ክርስቲያኑን በር በመቆለፍ አባ ግርማ የተባሉት መነኩሴ በዕለተ ሰንበት የክህነት አገልግሎታቸውን ትተው ከሴኩሪቲዎቹ ጋር በር ላይ በመቆም የእግዚአብሔር ቤተ መሆኑ ቀርቶ ልክ እንደ ግል ቤታቸው እከሌ ይግባ፤ እከሌ አይግባ በማለት ለጸሎትና ለቅዳሴ የሚመጣውን ሰው ማመስ ጀመሩ።

ይህ የሆነው ምንም ዓይነት ቅዳሴ የሚባል ሳይጀመር ነው። ቀጥሎም የተከለከሉቱና የታገዱት ሰዎች ሳይሆኑ ቀድመው ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ለጸሎት ደርሰው ከነበሩት ውስጥ ይህንን ታይቶም ተሰምቶም የማይታወቅ ክርስቲያናዊ ያልሆነ ተግባር በአባ ግርማና በተባባሪዎቻቸው ሲፈጸም እያዩ መታገስ ስላቃታቸው በሩን ክፈቱ በማለት እንደውም አንዲት የቤተ ክርስቲያን ቅን አገልጋይ ሴት ከውስጥ በኩል ከአባ ግርማ ጋር የበር ቁልፍ ይዛ ከቆመችው የባዕድ

ሴኩሪቲ ላይ ቁልፉን በመንጠቅ የተዘጋውን የእግዚአብሔር ቤት በር በርግዳ ከፈተችው።

ከዛም ከውጪ ተከለከሉ የተባሉት ሰዎች ሳይቀር ሲገቡ እነ አባ ግርማ ሁሌም እንደሚያደርጉት በቤተ ክርስቲያኑ ውስጥ የሚገኘውን የድምጽ ማጉያ በቁጥጥራቸው ስር በማድረግ ያንን ተጠቅመው የሃሰት መልዕት ለሕዝብ በማስተላለፍ ሕዝቡ እርስ በእርሱ እንዲበጣበጥ ለማድረግ ሲሞክሩ፤ የእነ አባ ግርማን ተንኮል ቀድመው የተረዱ ምእመናን በሕዝብ መካከል መወናበድ ሳይኖር የእነ አባ ግርማን በደልና ክርስቲያናዊ ያልሆነ ተግባር ለማጋለጥ እንዲችሉ አንዲት በእጅ የምትያዝ የድምፅ ማጉያ ይዘው በመግባት በዛ በመጠቀም ችግሩ የተፈጠረበትን ምክንያት እውነተኛውን መልዕክት ለሕዝቡ ለማስተላለፍ በመቻላቸው በሕዝብ መካከል ሊያነሱት ያሰቡትን ሁከት ሊያከሽፉት ችለዋል።

የጽሑፉ ዓላማ ግን የድምጽ ማጉያ ተይዞ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ተገባ በሚል ሰዎች ቤተ ክርስቲያንን ደፈሩ ለማሰኘት ሆነ ተብሎ የተዘጋጀ በመሆኑ ሁኔታውን በሚገባ ላልተረዳ ሰው በእርግጥም ይመስላል፤ ነገር ግን ከፍተኛ የድምጽ ጉልበት ያለው በቤተ ከርስቲያን ውስጥ በቋሚነት የተተከለ የድምጽ ማጉያ ስላለ ያንን እንደመሣሪያ በመጠቀም ሕዝብን የሚያበጣብጥ ሥራ ለመስራት ሲሞከር የመጀመሪያው ቀን ባለመሆኑ ያንን ለመቋቋም ከቤተ

ክርስቲያኑ ስፋትና ትልቅነት አኳያ ሰዎች በድምጻቸው ብቻ ተናግረው መሰማት ወይም ማሰማት ስለማይችሉ ሌላ አማራጭ አልነበራቸውና ያችን ትንሽ በእጅ የሚትያዝ የድምጽ ማጉያ ተጠቅመው ሃሰትን በእውነት አጋልጠዋል። እንግዲህ ሃቁ ይህ ነው።

ሌላው በጣም የሚገርመው በጽሑፉ ላይ የተገለጸውና ብዙ ጊዜ ሕዝብን ለማሳሳት የሚሞከርበት የቅዱስ ሲኖዶስና የሃገረ ስብከት ጉዳይ  የችግሩ መንስዔና ምክንያት አድርጎ ለማቅረብ የሚደረገው ሙከራ ነው ነው። ይህ ግን ትላንትም ይሁን ዛሬ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የችግር መንስዔ ሆኖ አያውቅም። በየትኛውም መድረክ ላይ የቤተ ክርስቲያኑ አባላት እንኳንስ ሊከፋፈሉበት ቀርቶ የቅዱስ ሲኖዶስና የሃገረ ስብከቱ ጉዳይ ተነስቶላቸው ተወያይተውበትም አያውቁም።

እንደውም የዛሬን አያድርገውና ቀደም ሲል ይህንን በምሥክርነት የሚያረጋግጡት ዛሬ ሕዝበ ክርስቲያኑን ለማሳሳት የቤተክርስቲያኑ ችግር በቅዱስ ሲኖዶስና በሃገረ ስብከቱ ምክንያት ነው በማለት መጻፍ ከጀመሩት መካከል አንዱ የሆኑት ቄስ አባተ በኢሳት ቴሌቪዥን ላይ ቀርበው ስለ ኤምባሲም ሆነ ስለ ሃገረ ስብከት ጉዳይ የተናገሩትን ቀጥሎ ያለውን ሊንክ በመጫን ያድምጡ ይመልከቱ።

https://www.youtube.com/watch?v=2D31l5lBDYc

እንግዲህ እነሱ በተንኮን በተለወሰ ቃል ከሚያደናግሩን እኛ እራሳችህ እውነተኛ አባቶች ጽፈው ያስተላለፉልንን የቤተ ክርስቲያን መተዳደሪያ ደንብ ቃለ አዋዲውን እንመልከት።

መንበረ ጵጵስና ሃገረ ስብከት ምን እንደሆነና እንዴት እንደሚመሠረት በቃለ አዋዲ አንቀጽ ፫፰ ላይ የተደነገገ ደንብና ሕግ ያለው ሲሆን፤ በዛ ደንብ መሠረትም ሃገረ ስብከት የሚመሠረተው ከአጥቢያ ቤተ ክርስቲያንና ከወረዳ ቤተ ክህነት የሰበካ አስተዳደር ጉባኤ በተውጣጡ ካህናት፤ ምእመናን እና የሰንበት ት/ቤት ወጣቶች አማካኝነት በሚመሠረት የሃገረ ስብከት የሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ አማካኝነት መሆኑን በግልጽ ተመልክቷል።

ሃገረ ስብከት ከተመሠረተ በኋላም የየአጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት ከገቢያቸው 20% ለሃገረ ስብከቱ እንዲገባ ያደርጋሉ። *ይህም በቃለ ዓዋዲው አንቀጽ ፩፪ ቁጥር ፩፪ ላይ ተደንግጎ የሚገኝ የቤተ ክርስቲያን ሕግ ነው።*

ዛሬ አባ ግርማና መሠሎቻቸው ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የገባውና በድንኳን ውስጥ ያለው በማለት ሕዝብን ለመከፋፈል ካልሆነ በስተቀር አሁንስ ቢሆን እነሱ ለፕሮፓጋንዳና ሕዝብን ለመከፋፈያነት እንጂ የትኛውን የቃለ ዓዋዲ ድንጋጌና ደንብ ተግባራዊ አድርገው ነው ቤተ ክርስቲያኗ በሃገረ ስብከቱ ሥር ነች እያሉ የሚለፍፉት?

በአቡነ እንጦስ ሊቀ ጳጳስነት የሚመራው ሃገረ ስብከት ከተመሠረተ ከ8 ዓመታት የተቆጠሩ ሲሆን ርዕሰ አድባራት ለንደን ደብረ ጽዮን ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን ግን በሃገረ ስብከቱ ውስጥ አንዳችም ተወካይ የላትም፤ ተሳትፋም አታውቅም፤ ሊቀ ጳጳሱም የቤተ ክርስቲያኑን ደጃፍ ረግጠው አያውቁም። ይህ የተረጋገጠ ሃቅ ነው።

ይህ የሆነበትም ከአባ ግርማ ጀምሮ የቤተ ክርስቲያኑ አባላት ባስተላለፉት ውሳኔና ዓለም በሚያውቀው አቋማቸው ጸንተው የኖሩ በመሆናቸው ከዛሬ 9 ዓመት በፊት አቡነ እንጦስ በአባ ጳውሎስ ተሹመው ሲመጡ የርዕሰ አድባራት ለንደን ደብረ ጽዮን ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያንን የአቋም መግለጫ ይቀበሉ እንደሁ ተጠይቀው አልቀበልም፤ አሻፈረኝ በማለታችው የተደመደመና ያለቀ ጉዳይ ነው።

ይህ ሕዝብ የወሰነው ውሳኔና የወሰደው አቋም ግን የእግዚአብሔር ቃል ባለመሆኑ አይለወጥም ማለት አይደለም፤ የሚለወጠው ግን ውሳኔውን ባስተላለፈው የቤተ ክርስቲያኑ አባላት ሌላ ውሳኔ ብቻ እንጂ አባ ግርማ ሥልጣኔን ይቀናቀኑብኛል ብለው ሲያስቡ አቡነ እንጦስን የቤተ ክርስቲያኗን በር ቢረግጡ አሳር ይጠብቅዎታል ብለው መልዕክተኛ እንዳላኩባቸው፤ አሁን ደግሞ ስልጣኔን ለማቆየት ያስችለኛል ብለው ሲገምቱ ተገልብጥው ወደ ኤምባሲ ሄደው መመሪያ በመቀበል ቤተ ክርስቲያኗ በሃገረ ስብከቱ ሥር ነች በማለት አቡነ እንጦስን ወደ ቤተ

ክርስቲያኗ ጎትተው ስላመጡ የሚሆን አይደለም። ይህንንን እውነታ አቡነ እንጦስ አጥተውት አይደለም ነገር ግን የሚፈለገው እውነት ሳይሆን ሥልጣንና ንብረት ስለሆነ ነው።

በዚህ መሠረት ከቄሱ የጳጳሱ እንዲሉ፤ ብጹዕ የተባሉት አቡነ እንጦስም ጥቂት ካህናት ለሥልጣንና ለንዋይ ሲሉ በፈጠሩት ችግር ቤተ ክርስቲያን ሰላም አጥታ ስትታመስ፤ በመጀመሪያ እሳቸው በተቀመጡበት ወንበር የነበሩትና እሳቸው የጫኑትን ቆብ ጭነው የነበሩት የቀደሙት እውነተኞቹ አባቶች እንደሚያደርጉት ለማንም ሳይወግኑ ድንጋይ ተሸክመውም ቢሆን እንደማስታረቅና ሰላምን እንደማምጣት፤ ይህ ካልሆነላቸው ደግሞ ሰላም ያወርድ ዘንድ ተንበርክከው ፈጣሪን በጸሎት መለመን ሲገባቸው እሳቸው ግን ጸቡና መከፋፈሉ ሳይበርድና ሕዝበ ክርስቲያኑ ተመልሶ አንድ ሳይሆን እግሬን ላስገባ በሚል ብልጣብልጥነት መንበሬን ወደ ማርያም ቤተ ክርስቲያን አዛውሬአለሁ የሚል አዋጅ በማሰማት ማደሪያችውና መኖሪያቸውም በእግዚአብሔር ተራዳኢነት በሕዝብ ገንዘብና ጉልበት በተገዛ የመኖሪያ ቤት (የቪካሬጅ ህንፃ) ውስጥ እንዲሆን የመኝታ አልጋቸውን ለማስገባት የሚጣደፉ ሆኑ።

ይህ ዓይነቱ ተግባር ሃይማኖትንና ቤተ ክርስቲያንን የሚያረክስ ካልሆነ በስተቀር የሃገረ ስብከት አመሠራርት

ነው የሚል በአንዳችም የቤተ ክርስቲያን ሕግጋት ላይ ታይቶም ተሰምቶም አይታወቅም።

ይህ በቤተ ክርስቲያኑ ቅጥር ግቢ ውስጥ የሚገኝ የመኖሪያ ቤት ደግሞ በሕዝብ ሃብትና ጉልበት መገዛቱ ብቻ ሳይሆን በውጪ ሃገር የተወለዱና የሚያድጉ ህጻናትና ወጣቶች ኢትዮጵያዊነታቸውን፤ ሃይማኖታቸውንና ባህላቸውን እንዲያውቁ በዛም ተኮትኩትው እንዲያድጉ ከመቶ ሺህ ፓውንድ በላይ ከሕዝብ በተውጣጣ ገንዘብ ታድሶ ለትምሕርት ቤትነት አገልግሎት ይውል ዘንድ ልዩ ልዩ ተጨማሪ ነገሮች እንዲሰሩበት የተደረገ ሲሆን ይህንን ትውልድን መተኪያ ማዕከል ነው ትምሕርት ቤትነቱ ቀርቶ መኖሪያ ቤታችው ሆኖ እንዲቀር አቡነ እንጦስ የተጣደፉት። ይህ ታዲያ ምን ዓይነት የጉድ ዘመን ላይ ደረስን አያሰኝም?

አቡነ እንጦስ አባ ግርማ ምን ዓይነት ሰው እንደሆኑ፤ በሚገባ ያውቃሉ፤ ምን ዓይነት ሥነ ምግባርና ምን ዓይነት ጭካኔ እንዳላቸው በሚገባ ይረዳሉ፤ ሌላው ቢቀር ለ7 ዓመታት በሳቸው በራሳቸው ላይ ያደረሱባቸው በደል የሚረሳቸው አይደለም፤ ነገር ግን ማርያም ቤተ ክርስቲያንን ከነንብረቷ ለመውረስ የቋመጡት አቡነ እንጦስ ለጊዜው መሸጋገሪያ ድልድያቸው አባ ግርማ ናቸው ብለው ስለሚያምኑ አባ ግርማን አሁንም ድረስ አቅፈው ደግፈው በመያዝ፤ በሌላ ሰው ይተኩ የሚለውን የአቅሌሲያን

እንቅስቃሴ እንኳ በቀጥታና በተዘዋዋሪ በማሰናከል ላይ እንደሚገኙ ለማወቅ ተችሏል።

ሌላው ቀርቶ አቡነ እንጦስ የቤተ ክርስቲያን አስተዳደር ይከበር፤ የቤተ ክርስቲያን አባላት ድምጽ ይሰማ፤ ሃሰትና ተንኮል ከእግዚአብሔር ቤት ይውጣ ብሎ ለእውነት የቆመውን ሕዝብ መንፈሳዊ አገልግሎት ከመሥጠት በስተቀር አንድም ጊዜ በተነሳው ውዝግብ ውስጥ ገብተው የማያውቁትን ቄስ ብርሃኑ ብሥራትን በደብዳቤ ጋጋታ ከማስፈራራት አልፈው በመጨረሻ ክህነታቸውን አንስቻለሁ እስከማለት የደረሱት አባ ግርማ በስልክና በአካል እየተገኙ የሚወተውቷቸውን የቄስ ብርሃኑን አውግዝልኝ ጥያቄ በመፈጸም አባ ግርማን ደልለው የማርያም ቤተ ክርስቲያን ቁልፍ በእጃቸው ለማስገባት እንደሆነ ገሃድ ከወጣ ውሎ አድሯል።

አቡነ እንጦስ ግን አባ ግርማ አቡነ እንጦስን ተጠቅመው የቤተ ክርስቲያኑን አባላት አሸንፈው ባለንብረት ለመሆን እንጂ በንብረቱ ላይ ያለውን ስማችውን ለአቡነ እንጦስም ሆነ ለሌላ ቢያዛውሩ እንደ እራፊ እቃ ተወርውረው እንደሚጣሉ ስለሚያውቁ ይህንን መቼም ቢሆን ሊያደርጉት የማይችሉ መሆኑን አለመገንዘባቸው ነው።

ቤተ ክርስቲያኗ እነ አባ ግርማን ጨምሮ 8 የሰበካ አስተዳደር ጉባኤና ሌሎች ልዩ ልዩ ንዑሳን ኮሚቴዎች ተመርጠው ከ5 ዓመት በላይ የሰሩበት፤ ህንፃ ቤተ

ክርስቲያኑን ለመግዛትና ቤተ ክርስቲያኑን ለከፍተኛ ዕድገት ደረጃ ለማብቃት ያስቻለ የውስጥ መተዳደሪያ ደንብ አላት፤ ይህንን ደንብ ግን ዛሬ እነ አባ ግርማ አናውቀውም በማለት በሕግ ፊት ክደውታል፤ ከቶ የእነ አባ ግርማ ተከታዮች ይህንን እና ሌላውን እነ አባ ግርማ በጠበቃቸው አማካኝነት የሚያቀርቡትን የሃሰት መረጃ ያውቁት ይሆን? እያወቁ ከሆነ እንዴት ሃሰተኛ መሆንን እና ሃሰትን መደገፍ እንደመረጡ በእጅጉ የሚያስገርም ነው።

ለዚህ ጽሑፍ መነሻ የሆነን የእነ አባ ግርማ ጽሑፉ በውጪ በድንኳን ውስጥ ስለሚጸልዩት ካህናትና ምእመናን ሲናገር፤ ሃጢአተኞች እንደሆኑ ለማሳየት ይሞክራል፤ በማያያዝም አንዳንድ ሰዎችን ጠልተው ነው በማለት ያትታል።

ማን ሃጢአተኛና ማን በደለኛ እንደሆነ፤ ማን በተንኮል ሕዝብን እየከፋፈለ፤ ለማፋጀት እንደሚጥር እግዚአብሔር ያውቀዋል፤ ለነገሩ ለጊዜው ነው እንጂ ግር የሚለው የውሸቱ ሰለባ የሆኑ ሰዎች ሳይቀሩ ነገ እውነቱ ግልጽ ብሎ ይታያቸዋል፤ አሁንም ማየት እንደጀመሩ ብዙ ምልክቶች አሉ።

በድንኳን ውስጥ የሚጸልዩት ካህናትና ምእመናን በመጀመሪያ ኢትዮጵያውያን ሲሆኑ ርዕሰ አድባራት ለንደን ደብረ ጽዮን ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያንን ከመመሥረት ጀምሮ አሥር፤ ሃያ፤ ሰላሣ አመትና ከዛም

በላይ ያገለገሉና የተገለገሉ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ እምነት ተከታዮችና ናቸው።

በድንኳን ውስጥ ለመጸለይ የመረጡበትም ምክንያት አምነው መርጠው ሾመዋቸው ክህደት ከፈጸሙባቸውና በውሸት፤ በቅጥፈትና በአጸያፊ ሥነ ምግባር ሃይማኖትንና ቤተ ክርስቲያንን ባረከሱ፤ ከበደላቸውና ከሃጢአታቸው በንስሃ ሳይጸዱ ቂምና በቀልን፤ ጥላቻና ተንኮልን እንዳዘሉ ባሉ ጨካኞች ላለመባረክና ከነሱም ጋር ላለመጸለይ ነው።

ይህ ብቻም አይደለም እንኳንስ ከካህን ቀርቶ ከማንም ተራ ሰው በማይጠበቅ ሁኔታ ለምን እኔን አልተከተልክም በማለት እግዚአብሔርን ረስተው ሰው አየኝ አላየኝ በማለት ተገላምጠው ቤተ ክርስቲያን በሚሳለም ምእመን ላይ ምራቅ የሚተፉ በእንደ እነ አባ ግርማ ዓይነት ካህን መባረክ ቀርቶ እንደነዚህ ዓይነቱ ካህናት የጌታን መስቀል በእጃቸው መንካታቸው እንኳ ስለሚያሰቅቃቸው ነው።

አዎ ይህንን የአባ ግርማን አፀያፊ ተግባር ያልሰሙና ያላወቁ ክርስቲያኖች እውነት ላይመስላቸው ይችላል ነገር ግን ቤተ ክርስቲያን ሲሳለሙ አባ ግርማ ምራቅ የተፉባቸው ሰው በህይወት አሉ፤ በአባ ድርጊት ምክንያት ለጊዜው አዘኑና መንፈሳቸው ተጎዳ እንጂ ከቤተ ክርስቲያናቸው አልቀሩም፤ ከዚህ በተጨማሪም አባ ግርማ ድርጊቱን ሲፈጽሙ እንኳን ከእግዚአብሔር ከሰውም አላመለጡም ይህንን አፀያፊ ነገር

ሲፈጽሙ ያየ ምሥክር በህይወት አለ ቆሞ መመሥከር ይችላል።

ሌላው ውሸትን እውነት አስመስሎ በማውራትና በማስወራት ሕዝብ ሆድና ጀርባ እንዲሆን አድርገው፤ እስከ ደም መፋሰስ ካደረሱ በኋላ ያ ጥላቻና ቂም በቀል በይቅር ለእግዚአብሔር ሳይደርቅና ሳይሽር ቤተ ክርስቲያኑን ቀድመን ብንከፍት አሸናፊ እንሆናለን በሚል ግብዝነት ተነሳስተው የሰው ልብ እንደተዘጋ የቤተ ክርስቲያንን በር በተንኮልና በሸር በመክፈታቸው ነው።

ይህም ድርጊታቸው በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የጎሪጥ ከመተያየት ባለፈ ጸብና አንባ ጓሮን የሚጋብዝ በመሆኑ፤ ቤተ ክርስቲያንን እንደገና ሌላ ዙር የብጥብጥና የሁካታ ቤት ላለማድረግ እና በሌላ በኩል ደግሞ በደለኞቹ በአስተዳደር ወንበር ላይ ያሉት ካህናት ሆነው ከሌላውና ከማይመለከተው ክርስቲያን ወንድምና እህት፤ እናትና አባት ጋር ክርስቲያናዊ ያልሆነ አታካራም ሆነ ታሪክ ይቅር የማይለው መጎዳዳት እንዳይፈጠር ለማድረግ ሲባል የቤተ ክርስቲያኑ አባላት ፍትሕን እስኪያገኙ ድረስ ዝናብ፤ ብርድና ቁር እየተፈራረቀባቸው በውጪ ጸሎታቸውን በማድረግ ላይ ይገኛሉ።

ቤተ ክርስቲያን የእግዚአብሔር ቤት ናት ማንም በሯ ላይ ቆሞ አንተ ግባ አንተ አትግባ አይልባትም፤ በክርስቶስ የተጠመቀና ያመነ ሁሉ ገብቶ የሚገለግልባት ናት፤ እውጪ

በድንኳን ውስጥ የሚጸልዩትም ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ለመግባት ማንም አይከለክላቸውም፤ በኤምባሲ ተቀጥረው በር ላይ የሚቆሙት ሴኩሪቲዎችም ማንንም የማስቆምም ሆነ የልብሱን ጫፍ የመንካት መብት እንደሌላቸው ሁሉም ያውቃል።

ይህም በመሆኑ በውጪ የሚጸልዩት መቶና ሁለት መቶ ሰው ቀርቶ አስር ሰውም መብቴ ተነካ ብሎ ካመነ መብቱን ለማስከበር ተቃውሞ ማንሳት ይችላል ነገር ግን በነዚህ ቤተ ክርስቲያንን ባረከሱና የአስተዳደር በደል በፈጸሙ ላይ ተቃውሞ ከማንሳትና እነሱ የሚፈልጉትን በሕዝበ ክርስቲያኑ መካከል ብጥብጥ ከመቀስቀስ ይልቅ የተፈለገው ችግር ይድረስብን፤ ጉዳዩ በሕግ እልባት እስሚያገኝ በውጪ እንቆያለን በማለት እግዚአብሔር የሚወደውን የሰላሙን መንገድ በመከተል ጸንተው ስለሚገኙ ይህም ቀና አስተሳሰብ ጽናት ጥንካሬና ፍቅር ሰጥቷቸው በደስታ የሚፈለገውን መስዋዕትነት ሁሉ በመክፈል ላይ ይገኛሉ።

በውጪ በድንኳን ውስጥ የሚጸልዩት ካህናትና ምእመናን እነ አባ ግርማ እንደሚሉት ወደ ቤተ ክርስቲያን የሚገባውን ሕዝብ በጠላትነት የሚያዩት አይደሉም፤ ሊያዩትም አይገባም፤ ነገ እውነት ወጥቶ ፍትሕ ሲገኝ፤ የከፋፍዮች ዓላማ ሲከስም ይህ ሕዝብ በአንድ ጣሪያ ሥር ሆኖ ፈጣሪውን ማምለኩ የማይቀር ስለሆነ ትርፉ ትዝብት ነው። አንዳንድ በግለሰብ ደረጃ የሚደረግ የስድብና የመጥፎ

ቃላት ልውውጥም ቢኖርም ይህ በስሜታዊነት የሚመጣ ስለሆነ ጨርሶ መቅረትና መወገድ ያለበት ነው።

ከዚህ ውጭ ግን የእነ አባ ግርማን ሕዝብን የመከፋፈልና የማበጣበጥ ዓላማ በመያዝ ከግለሰብ አልፈው በነጭ ድንኳን ውስጥ ያሉ ወዘተ.. በማለት ሕዝብን የሚሰድቡ፤ ሕዝበ ክርስቲያኑን ለማዋረድና ለማራከስ የሚጥሩ፤ የክርስቲያኖች እርስ በእርስ መቃቃር ሰርግና ምላሽ የሆነላቸው የክርስትና እምነት ተከታዮች ቀርቶ ኢትዮጵያዊ መሆናቸውን ለማመን ያሚያዳግቱ የስድብና የብልግና ንግሥናን የተቀዳጁ የሚመስሉ ግለሰቦች መታየት ጀምረዋል፤ እነዚህ ሰዎችም በእነ አባ ግርማ አሞካሽነትና አበረታችነት እንደሚንቀሳቀሱ ይታወቃል፤ ነገር ግን ነገ የእውነት ፀሐይ ሲወጣ እነዚህን ግለሰቦች አባ ግርማም ሆኑ ሌሎች አይዞህ ባዮቻቸው ከሰማይ ቁጣም ሆነ ከምድራዊ ፍርድ አያድኗቸውምና ለራሳቸውም ሆነ ለቤተ ሰቦቻቸውና ለታሪካቸው መልካም ስራን ለመስራት ቢሞክሩ ይበጃቸዋል።

ወስብሐት ለእግዚአብሔር! አሜን።

አሰፋ ምን ተስኖት